# ሰበር ዜና

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ከይስሙላው ምርጫ 2002 እለት ጀምሮ ምርጫው ሙሉ በሙሉ በጠራራ ጸሐይ መጨበርበሩንና ወያኔ/ኢሕአዴግ አሸንፊያለሁ ያለውንም በጭራሽ እንደማይቀበል በይፋ መግለጹ ይታወሳል።

ከዚያም በሕግ በኩል ተጨባጭ ማስረጃዎቹን ይዞ እስከመጨረሻው የሕግ አካል ድረስ በመክሰስ ምንም እንካን ውጤት ባያመጣም የወያኔ የሕግ አካል ለማን እንደቆመም ፈትሾ አጋልጡዋል።

በቅርቡ ደግሞ መኢአድ በከተማም በገጠርም ያሉትን አባላት በያሉበት ድክመትና ጥንካሬያቸውን እንዲገመግሙ በማድረግ የግምግማውን ውጤት አሰባስቦ ጨርሶዋል።

ከዚህ ቀጣዩ ደግሞ መኢአድ በምን አቅጣጫ ትግሉን መምራትና መታገል እንዳለበት ተወያይቶ ያንን ለሕዝብ ለማሳወቅ ማክሰኞ ነሀሴ 18 ቀን 2002 ዓ/ም ለውስጥና ለውጭ የሚዲያ ሰዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ይሰጣል። ከድርጅቱ የሚሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫም በድህረ ገጻችን ላይ እናወጣለንና እንድትከታተሉ አስቀድመን እናስታውቃለን።

የመኢአድ ድጋፍ በካናዳ

This document was created using Smart PDF Creator
To remove this message purchase the product at www.SmartPDFCreator.com